ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

ፕሮግራም፡ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 13 ሜትር ባንድ

Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on n25 meter band

**ታህሳስ 19 ቀን 2006 ዓ.ም.**

**December 28, 2013**

**ሁለት ከፍተኛ የብአዴን ባለስልጣኖች ድንገት ተባረሩ**

**የወያኔ ባለስልጣናት መሀከል የተጀመረው የመጠላለፍ ፖለቲካ ውጤት ነው ተባለ**

በጭንቀት እና በውጥረት... በሴራና በመጠላለፍ....በተንኮል እና በሸር...ተወታትቦ እየታመሰ የሚገኘው የወያኔ ቡድን በአንድ ሳምንት ውስጥ ሶስት ከፍተኛ ባለስልጣናትን ከኃላፊነታቸው ማንሳቱ በአባሎቹ ጭምር መነጋገሪያ ሆኖ ሰነበተ፡፡

በወያኔ አባላት መሀከል የተጀመረው ጉሽማ ለብአዴንና ለሌሎቹ ተለጣፊ ድርጅቶች እድል ሰጥቷል ተብሎ በተወራ በጥቂት ወራት ውስጥ የወያኔ አባላባት የውስጥ ችግሮቻቸውን ለግዜው ወደ ጎን በማድረግ በወሰዱት የመልሶ መቆጣጠር ዘመቻ በአሁኑ ወቅት የብአዴን ነባር ሰዎች እያንሳፈፏቸው መሆኑ በይፋ ተነግሮዋል፡፡

የአማራ ክልል ፕሬዝዳንት ሆኖ ከ10 ዓመት በላይ ያገለገለው እና ከመለስ ጋር እሳት እና ጭድ ሆኖ የነበረው አያሌው ጎበዜ ባሕር ዳር ከተማ ተደረገ በተባለ ግምገማ መረረኝ...ሰለቸኝ...አቃተኝ ብሎዋል በሚል ከስልጣኑ የተነሳ መሆኑ ታውቆዋል፡፡

ነባር የኢህዴን/ብአዴን ታጋይ ናቸው ከተባሉት መሀከል አንዱ የነበረው ይሄው የአማራ ክልል ፕሬዝዳንት ሆኖ ለብዙ ዓመታት ወያኔ ሲያገለግል የቆየው አያሌው ጎበዜ በወያኔ ባለስልጣናት ዘንድ በበጎ አይን የማይታይ እንደነበርና በአንድ ወቅት ለሶስት ወራት በቁም እስር ላይ እንዲቆይ ተደርጎ የነበረ መሆኑ የሚታወስ ሲሆን በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተቃውሞ በማድረጉ በወያኔ ባለስልጣናት ክፉኛ ጥላቻ ውስጥ ገብቶ እንደነበርና ከስልጣኑ እስከተወገደበት ባለፈው ሳምንት ድረስ በአይነ ቁራኛ ሲጠበቅ የቆየ መሆኑን ቅርበት ያላቸው ወገኖች ተናግረዋል፡፡

ሰሞኑን መተካካት በሚል ሰበብ በግምገማ የተነሳው አያሌው ጎበዜ በአንድ ወቅት ከጎንደር ተቆርሶ ለትግራይ የተሰጡትን ወረዳዎች አስመልክቶ ተቃውሞ ማንሳቱ ሲነገር የቆየ ሲሆን በዚህ ምክንያት በተለይ ከሁለት ዓመት በፊት ከማንም ሰው ጋር እንዳይገናኝ ተከልክሎ ከስልጣኑ ተነስቶ ከባህር ዳር ወደ አዲስ አበባ መጥቶ በቅሎ ቤት አቅራቢያ ጠመንጃ ያዥ ጀርባ በአንድ ትልቅ ቪላ ግቢ ውስጥ ለሶስት ወራት በቁም እስር ላይ እንዲቆይ ተደርጎ እንደነበርና ይህንን ተከትሎ በብአዴን ነባርና አፍለኛ ካድሬዎች ዘንድ ቁጣ በመቀስቀሱ ከቁም እስር ሊለቀቅ መቻሉን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች ሲናገሩ ተደምጠዋል። ለሱዳን የሚሰጠውን መሬት አስመልክቶ ተመሳሳይ ተቃውሞ በማሰማቱ በባእዴን ባለስልጣኖች በአዲሱ ለገሰና በበረከት ስሞኦን እንዲሁም በወያኔ ባለስልጣናት ዘንድ በጥላቻ አይን ይታይ እንደነበር እነዚሁ ወገኖች ተናግረዋል፡፡ በዚህም መሰረት

ከብአዴን ስራ አስፈፃሚነት እንዲነሳ እና በማዕከላዊ ኮሚቴ ውስጥ ለይምሰል እንዲሳተፍ ተደርጎ የነበረ መሆኑን አስታውሰው የክልሉ ምክትል ፕሬዝዳንት እና የብአዴን ምክትል ሊቀመንበር የሆነውና ሁሉንም ትእዛዝ ለመፈጸም ዝግጁ የነበረው ገዱ አንዳርጋቸው የተባለው አፍለኛ ካድሬ ስልጣኑን ሙሉ ለሙሉ ከዓመት በፊት ተረከቦ እንደነበር በተጨማሪ ገልፀዋል፡፡

ኢህዴን/ብአዴን ለማን ነው የቆመው በሚል በአንድ ወቅት የብአዴን አፍለኛና ነባር ካድሬዎች እነ በረከትን በጥያቄ ሲያፋጥጡ ከነበሩት ባለስልጣናት መሀከል አንዱ አያሌው ጎበዜ ነበር ይባላል።

በአንድ ሳምንት ውስጥ በተደረገው የምንጠራ ዘመቻ ሁለት የብአዴን ነባር ሰዎች የተንሳፈፉ ሲሆን ከአያሌው ቀጥሎ የማዕድን ሚኒስቴር ሚኒስትር የሆነችው ስንቅነሽ እጅጉም ሳይነገራት እና ሳትሰማ ከስራ ተመልሳ እቤትዋ እንዳለች በቴሌቪዥን ከሚኒስትርነት ማእረግ የተነሳች መሆኑን መስማትዋንም ለቤተሰቦችዋ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል፡፡

እንደማንኛውም ዜጋ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በዜና እወጃ ላይ ከሚኒስትርነትዋ መነሳትዋን የሰማችው ይህችው ሴት በድንጋጤ በመኖሪያ ቤትዋ እራስዋን ስታ እንደነበርና ለሰዓታት በክሊኒክ ቆይታ አድርጋ ሊሻላት እንደቻለ የታወቀ ሲሆን ከዚያን ግዜ ጀምሮ ወደ ቢሮዋ ሳትገባ እንደቆየችና ቦታው በሌላ ሰው ወዲያውኑ መያዙ ታውቋል፡፡

ይህችው ስንቅነሽ እጅጉ የተባለችው የብአዴን ከፍተኛ ካድሬ ለኮታ ማሙያ ተብላ በሚኒስትርነት ተቀምጣ የቆየች ቢሆንም የወያኔ ባለስልጣኖች በጀመሩት ብአዴንን ቀስ በቀስ የማዳከም ተግባር አንደኛዋ ተሰናባች የተደረገች ሲሆን የብአዴን ካድሬዎች ተቃውሞ እንዳያሰሙ ለማድረግ አያሌውም ሆነ እስዋ በአምባሳደርነት የተሾሙ መሆኑ በዜና እወጃ ቢነገርም ለየትኛው ሀገር... ከመቼ ጀምሮ የሚሉት ምላሽ ያላገኙ ጥያቄዎች መሆናቸውም ታውቆል፡፡

በጎንደር ለም መሬት ሽያጭ ላይ ሰፊ ተሳትፎ የነበረውና የመለስን ትዕዛዝ ያለሽርፍራፊ ሲያስፈጽም የቆየው የብአዴን ምክትል ሊቀመንበር የነበረው ደመቀ መኮንን ሀሰን ለዋለው ውለታ ከአዲሱ ለገሰ የሊቀመንበርነቱን ስልጣን በተቆጣጠረ በአጭር ግዜ ውስጥ ከትምህርት ሚኒስትርነቱ በተጨማሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ የተሾመ መሆኑ ይታወሳል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በአያሌው ጎበዜ ምትክ የክልሉን ፕሬዝዳንትነት ምክትሉ ገዱ አንዳርጋቸው የተባለው ካድሬ የተረከበ ሲሆን ግለሰቡ የክልሉ የግብርና ቢሮ ኃላፊ... የብአዴን ምክትል ሊቀመንበር መሆኑም ለማረጋገጥ ተችሎዋል፡፡

በዚሁ ሰሞን ደግሞ የአማራ ብሔር ተወላጅ ሆኖ ለ20 ዓመታት የወያኔን ቡድን በምክትል ሚኒስትርነት እና በሚኒስትርነት ሲያገለግል የቆየው የቀድሞው የኢኮኖሚና ልማት ሚኒስትር የአሁኑ የፕላኒግ ኮሚሽን ኮሚሽነር መኮንን ማንያዘዋል በዓለም ዓቀፍ ስብሰባ ላይ ተጋብዞ ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ እንዳይሄድ የተከለከለ መሆኑ ታውቆዋል፡፡

ባለፈው ሳምንት ውስጥ ከሁለቱ ነባር የወያኔ ባለስልጣናት በተጨማሪ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስኪያጅ ሆኖ ለብዙ ዓመታት ሲሰራ የነበረውና የአዜብን እህት ያገባው ምህረት ደበበም ተደረገ በተባለ ግምገማ መሰረት ብቃት የለውም ... ሰራተኛውን መምራት አልቻለም...ከጥቅሙ ጉዳቱ አመዝኖዋል...በሚል በደብረጽን ተዘልፎ ከስልጣኑ የተባረረ መሆኑ ታውቋል፡፡

**በቅርቡ ወያኔ የሌ/ጄ/ልነት ማዕረግ የሰጠው የወያኔው ታጋዩ ዮህንስ ገ/መስቀል ኤታማዦር ሹም ሊሆን ይችላል ተባለ**

በጭንቀት እና በፍርሀት ተወጥረው ከነገ ዛሬ ምን ይፈጠራል ብለው የሚገኙት የወያኔ ባለስልጣናት የመከላከያ ሰራዊቱን አዛዦች የራሳቸው ደጋፊ ለማድረግ ውስጥ ውስጡን ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረጉ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ጄ/ል ሳሞራ የኑስ እና በስልጣን ላይ የሚገኙ ጥቂት የወያኔ ሰዎች ሀገሪቱን እያመሱ እንደሚገኝ ተጋለጠ፡፡

በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የኢኮኖሚ ክላስተር አስተባባሪ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስትሩ በሆነው በወያኔው በደብረጽን ወልደሚካኤል የሚመራው አንዱ የወያኔ አንጃ ከወያኔ ሰዎችም ሆነ ከሌሎቹ ተለጣፊ ድርጅቶች በላይ በመሆን ከ ሳሞራ የኑስ ጋር ሀገሪትዋን እያመሱዋት መሆኑን የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ፡፡

የወያኔ ባለስልጣናት የእርስ በርስ ሽኩቻ ውስጥ ባሉበት በዚህ ወቅት የወያኔው መከላከያው ኤታማዦር ሹም ጄ/ል ተብየው ሳሞራ የኑስ ከኃይለማርያም ደሳለኝ እውቅና ውጭ የጦሩን የበላይነት በጥቅምና በኃይል ጭምር ተቆጣጥሮ ለመያዝ የሚያደርገው ሩጫ በተወሰነ መልኩ እየተሳካለት መሆኑን ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ተናግረዋል፡፡

በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተብየው በደብረጽን ወ/ሚካኤል የሚመራውና... ሳሞራ የኑስ ...በደህንነቱ ጌታቸው አሰፋ.... እንዲሁም በአዲሱ የመረጃ ደህንነት መረብ ኃላፊ በብ/ጄ/ል ተብየው በተክለብርሀን አረጋዊ የሚደገፈው ይሄው የወያኔ አንጃ በየቀኑ ከምሽቱ ስድስት ሰዓት በሁዋላ በምስጢር እየመከረ ከመሆኑም በላይ የአንጃው አባላት አብዛኛው የወያኔ ባለስልጣናት የማያውቁትን ውሳኔ እያሳለፉ በመሆናቸው በቡድኑ ውስጥ ግራ መጋባት እየተስዋለ እንደሚገኝ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጨምረው እየተናገሩ ይገኛሉ፡፡

መለስ በሕይወት በነበረበት ወቅት የአየር ኃይሉን ነጥሎ ለመቆጣጠር እንዲያስችለው በቀጥታ ከአየር ኃይሉ ዋና አዛዥ ሜ/ጄ/ል ሞላ ኃይለማርያም ጋር ሲገናኝ የነበረ መሆኑ የሚታወስ ሲሆን የመለስን መሞት ተከትሎ ሳሞራ ሜ/ጄ/ል ሞላ ኃይለማርያምን ያለ አንዳች ምክንያት ከአየር ኃይል አዛዥነቱ አንስቶ በአልባሌ ቦታ እንዲቀመጥና በምትኩ ደጋፊው የሆነውን የወያኔ ነባር ታጋይ ሜ/ጄ/ል ተብየው አደም መሀመድን መሾሙም ይታወቃል፡፡

በጡረታ ለቅቆ ስልጣኑን ለሳዓረ መኮንን ያስረክባል ተብሎ ሲጠበቅ የነበረው ሳሞራ አበባው ታደሰና ሳዓረ መኮንን ከነበሩበት የእዝ አዛዥነት ቦታ አንስቶ ለማእረጋቸው በማይመጥን ተራ መምሪያ እንዲቀመጡ ያደረገ ማድረጉና በምትካቸው ቅርቡ የሆነውን ዮሀንስ ገብረመስቀል የተሰኘውን የወያኔ የበረሀ ታጋይ የሌ/ጄ/ልነት ማዕረግ ሰጥቶ መሾሙ ለዚህ ግለሰብ የኤታማዦር ሹምነቱን ስልጣን ሊሰጠው እንደተዘጋጀ የሚያመላክት ፍንጭ ነው ሲሉ የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ይጠቁማሉ፡፡

በአሁኑ ሰዓት በሰራዊቱ ውስጥ የሚደረገውን ማንኛውም እንቅስቃሴ በብቸኝነት እየመራ የሚገኘው ሳሞራ የኑስ ሲሆን ከእነ ደብረጽን ጋር በምስጢር እየመከረ በሌሎቹ ባለስልጣናት ላይ ጫና እየፈጠረ  እንደሆነም ጉዳዩን በቅርበት ከሚከታተሉ ወገኖች የደረሰን ጥቆማ ያስረዳል፡፡

**በሳዑዲ አረቢያ የተፈጸመው ግድያና ወከባ በጁባም ተደገመ**

**ዑጋንዳና ኬንያ ሳይቀር ዜጎቻቸውን ሲያወጡ የወያኔ ቡድን ግን በዜጎቻችን ላይ እያላገጠ መሆኑ ተጠቆመ**

የወያኔ ቡድን በሚያካሄደው የፖለቲካ አፈና እና በሀገሪቱ በተከሰተው የኑሮ ውድነት ምክንያት ዜጎች እግራቸው ወደ አመራቸው ሀገር እየተጉዋዙ ኑሮ ብለው ቢጀምሩም ከቅርብ ግዜ ወዲህ እጅግ አስደንጋጭ የሆኑ አደጋዎች እየተከሰቱባቸው መሆኑ ታወቀ፡፡

በቅርቡ ለዓመታት ከኖሩበት ሳዑዲ አረቢያ እጅግ ቁጥራቸው የበዙ ዜጎች ሲገደሉ እና ሲደበደቡ እንዲሁም ሴቶቹ በቡድን ሲደፈሩ እድል ቀንቶዋቸው የተረፉት ደግሞ ባዶ እጃቸውን ተጠርዘው የተባረሩ ኢትዮጵያውያኖች የደረሰባቸው ግፍ እና መከራ ሳይቀዘቅዝ ሰሞኑን ደግሞ በተመሳሳይ በደቡብ ሱዳን ጁባ ከተማ ተከስቶዋል፡፡

ለብዙ ዓመታት ሰርተው ያፈሩትን ሀብት ንብረት በሀገሪቱ ወርሮ በላ ወጣቶች የተቀሙት እና ባዶ እጃቸውን ተጠርዘው ወደ ሀገር ቤት የተመለሱት በሳዑዲ አረቢያ ሲኖሩ የነበሩት ዜጎች ዋይታና ለቅሶ ሳይበርድ አሁን ደግሞ በተመሳሳይ ገና በቅርቡ እውቅና ባገኘችው ደቡብ ሱዳን ውስጥ በተከሰተ የእርስ በርስ ሽኩቻ ምክንያት ገሚሱ ሕይወቱ ሲያልፍ ገሚሱም ቆስሎ የሚያነሳው አጥቶ በየጉድባው ወድቆ መገኘቱን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

የደቡብ ሱዳኑን መሪ ሳልቫኪርን ለማጽናናት ወደ ጁባ ተጉዞ የነበረው የወያኔ ቡድን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቴዎድሮስ አድህኖምም   በስቃይ እና በሞት ላይ ያሉትን ዜጎች ሳያናግር እና መፍትሔ ሳይሰጣቸው የተመለሰ ሲሆን በአንጻሩ አብረውት የነበሩት የኬንያና የኡጋንዳ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ዜጎቻቸው ከጥቃት እና ከአደጋ ለመከላከል ሲሉ ወደ ሀገራቸው እንዲወጡ ማድረጋቸው ታውቆዋል፡፡

በጁባ በተለያዩ ስራዎች ላይ ተሰማርተው የነበሩት ኢትዮጵያውያኖች ያፈሩት ሀብትና ንብረት ሙሉ ለሙሉ ተዘርፎ የወደመባቸው ከመሆኑም በላይ በጥይት ተመትተው በየስርቻው ወድቀው የሚገኙት ኢትዮጵያን የህክምና ርዳታ ያላገኙ ከመሆኑም በላይ የሚቀምሱት ውሀ እና ምግብ አጥተው እየተሰቃዩ እንደሚገኙ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡